

# እግዚአብሔር ምን ያክላል?

20-2

## 4. እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃል

**“የእግዚአብሔርን መንፈስ የያዘ ወይንም አማካሪ ሆኖ ያስተማረው ማነው? ወይስ ከማን ጋር ተመካከረ ወይንም ማን መከረው? የፍርድንም መንገድ ማን አስተማረው? እውቀትንስ ማን አስተማረው የማስ ተዋልንስ መንገድ ማን አሳየው?”** (ኢሳያስ 40፥13 ና 14)። እግዚአብሔር የማያውቀው ነገር በዓለም ላይ አንድም የለም። ስለሆነም ማንንም ምክር አይጠይቅም። ከመላእክቶቹም መካከል ሊያማክሩት ወይም ሃሳብ ሊሰጡት የሚችሉ የሉም። እንዲሁም እግዚአብሔርን አዲስ ነገር ሊያስተምረው የሚችል ኃይል የለም። ስለ ሁሉም ነገር ያውቃል። እግዚአብሔር ከዚህ በፊት የማያውቀውን ነገር ልናሳውቀው አንችልም። እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃል ስንል አንድ የሚያሳስበን ነገር አለ። ይኸውም ምንም ያህል ትንሽም ብትሆን በጉስጉሻ ውስጥ የተደረገችም ብትሆን በልባችን ያሰብናትም ኃጢአት ብትሆን እግዚአብሔር የሚያውቅ መሆኑን ነው። ሃሳባችንን ያውቃል እቅዳችን ፍላጎታችንን አስቀድሞ ያውቃል። በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ማወቁ ደስ ያሰኘናል። ስለእኛ ስለ አለፈው ሕይወታችንም ሆነ ስለ አሁኑ ስለ ወደፊቱም እግዚአብ ሔር ያውቃል። ማንም ሰው ከዚህ በፊት ስለሠራነው ኃጢአት ሊከሰን የሚችል አይኖርም። ምክንያቱም አስቀድሞ እግዚአብሔር አውቆት ያለፈውን ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅርታ ያደረገልን መሆኑን ስለምናውቅ ነው። ሌላው ደግሞ እግዚአብሔር እለታዊ ፍላጎታችንን፣ ሃሳባችንን፣ ጭንቀታችንን፣ ችግራችንን ስለሚያ ውቅ ደስ ይለናል። ስለ ችግራችን፣ ሰለ ፍላጎታችንና ተስፋ ስለሚያስቀርጠን ነገር እግዚአብሔር የሚያ ውቅ መሆኑን መረዳት ምን ያህል የሚያጽናና እንዲሁም ድስ የሚያሰኝ ነገር ነው! ማወቅ ብቻ ሳይሆን እደፍላጎትችንና እንደችግራችን መጠን እርሱ ያገለግለናል። አስቀድሞ ወደ ፊት የሚጠብቀንን ነገር እርሱ ያውቃል። ስለዚህ በእርሱ መተማመን እንጂ መጨነቅ አይገባንም። በአስቸጋሪ መንገድ ሁሉ እንዴት እንደሚመራን ያውቃል። ስለዚህ ይህንን እግዚአብሔር እኔና እናንተ ልናመሰግነውና ሕይወታችንን ሙሉ በሙሉ ልንሰጠው ይገባል።

## 5. ኃይል ነው

**“ኃይል ሁሉ የእርሱ ነው፤ በእርሱም የሚኖሩት እንደ አንበጣ ናቸው፤ ሰማያትን እንደ መጋረጃ የሚ ዘርጋቸው እንደ ድንኳንም ለመኖሪያ የሚዘረጋቸው አለቆችንም እንዳልነበሩ የምድርንም ፈራጆች እንደ ከንቱ ነገር የሚያደረጋቸው እርሱ ነው። ገና እንደተተከሉና እንደ ተዘሩ በምድርም ሥር ገና እንደሰደዱ ወድያውኑ ነፈሰባቸው እነርሱም ደረቁ። አውሎ ነፋስም እንደ እብቅ ጠረጋቸው”** (ኢሳያስ 40፥22-24)። እግዚአብሔር በምድር ዙሪያ ሁሉ ይገኛል። በዓለምም ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በእግዚአብሔር ዓይን ሲታዩ እንደ አንበጣ ናቸው። ከእግዚአብሔር ጋር ስንወዳደር እኛ ሰዎች ምን ያህል ደካሞችና ትንንሾች እንደሆንን እናያለን። ይሁን እንጂ ብዙ ጊዜ ባደርግነውና ባከናወነው ነገሮች በልባችን እንኩራራለን። የሰው ኃይልና ጉልበት እንዲሁም በምድር ላይ ያከናወናቸው ነገሮች እግዚአብሔር ከሠራቸው ጋር ሲወዳደር አንበጣ ከቦታ ቦታ የሚያዘዋውራቸውን ሳሮችን ይመስላል። እርግጥ ነው የሰው ልጅ ከእግዚአ ብሔር በረከትን ስለተቀበለ ብዙ ነገሮችን ማወቅና ማግኘት ችሏል። በሕክምና ዓለም ከፍተኛ ክንውኖችን አድርጓል። ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ክንድ ጋር ሲወዳደር አሁንም የሰው ኃይልና የሰው እውቀት እንደ አንበጣ እውቀት ነው። አለቆችና የምድር ፈራጆች ከእግዚአብሔር ጋር ሲወዳደሩ ከንቱ ናቸው።

በእግዚአብሔር ላይ ተነስቶ እግዚአብሔርን ያሸነፈ እስከ አሁን ድረስ አልተገኘም። እርግጥ ነው ብዙዎቹ ሞክረዋል፤ ይሁን እንጂ ተሸንፈው ወድቀዋል። ኔሮ ሞክሮ ወድቋል። ሂትለር፣ እስታሊን ሌሎችም ተመሳሳይ ሙከራዎች አድርገው ተሸነፈው ወድቀዋል። እነዚህ ሁሉ እግዚአብሔርን ለማሳነስና ዝቅ ለማድረግ እራሳቸውን ደግሞ ትናንሽ እግዚአብሔሮች ለማድረግ ሞክረው ሳይሳካላቸው የቀሩ ናቸው።

በዓለማችን እራሳቸውን "ትናንሽ እግዚአብሔሮች" ለማድረግ የሞከሩ ብዙ ሰዎች አሉ። እግዚአብሔርን በመቃወም "ከሕይወቴ ውጣ፣ የራሴን ሕይወት ልኑርበት፣ በመንገዴ አትቁም" ሲሉ እግዚአብሔርን የተናገሩት ሰዎች ብዙ ናቸው። ይሁን እንጂ ሕይወታችን የተመሰረተው በእግዚአብሔር ምህረት ሥር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ማንም በእግዚአብሔር ላይ ተነስቶ የሚያሸንፍ የለም። አንድ ቀን ጉልበት ሁሉ ለእርሱ ይንበረከካል ምላስ ሁሉ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ይናገራል። ይህን የመሰለው የእግዚአብሔር ኃይል እኛን ክርስቲያኖችን አያስፈራንም፣ አያስደነግጠንም። በዚያ ፋንታ ግን የኃይላችንና የድፍረታችን ምንጭ ይሆንልናል። እግዚአብሔር ኃይል ካለውና ታላቅ ከሆነ ሊያድነን ይችላል ብለን መተማመን እንችላለን። የጨለማ ኃይል ከእርሱ እጅ ፈልቅቆ ሊወስደን እንደማይችል ስንረዳ ልባችን በሰላም ይሞላል። ብዙ ጊዜ ችግርና መራራ ልምድ በሕይወታችን ሲደርስብን እግዚአብሔር የረሳንና የተወን ይመስለናል። ይሁን እንጂ ኢሳያስ እንዲህ ሲል ያስረዳናል። **"እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው፤ አይደክምም፤ አይታክትም፤ ማስተዋሉም አይመረመርም። ለደካማም ኃይልን ይሰጣል። ጉልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል። ብላቴኖች ይደክማሉ፤ ይታክቱማል። ጎበዛዝቶች ፈጽመው ይወድቃሉ። እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ እንደ ንስር በክንፍ ይሮጣሉ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ፤ አይደክሙም"** (ኢሳያስ 40፥28-31)።

እግዚአብሔር ይህን ዓይነት አምላክ ከሆነ ይረሳናል ወይንም ይተወናል ብለን ልንፈራ አይገባም። እርሱ አይደክምም፤ አይታክትም፤ ትዕግስቱም አያልቅም። እርሱን በትዕግስትና በታማኝነት ለሚጠብቁ ሁሉ ኃይላቸውን ያድሳል። የአሸናፊ ሕይወት ቁልፍና ሚስጥሩ እርሱን በመጠበቅ ላይ ነው። ብዙ ጊዜ የራሳችን ችግር በራሳችን ጥረት በራሳችን ውሳኔና ኃይል ለማሻሻል እንሞክራለን። ይሁን እንጂ ብዙ ሳንራመድ ተደናቅፈን እንወድቃለን። እርዳታን ከእግዚአብሔር ከመፈለግ ፈንታ ዛሬስ አበቃሁ፤ የእኔ ሕይወት አከተመ ያልንበትና ተስፋ የቆረጥንበት ጊዜ ምን ያህል ይሆን? እግዚአብሔርን የሚጠብቁ፣ የሚወዱትና የሚያገለግሉት፥ ድካማቸውን ተገንዝበው እርሱን ወደ ሕይወታቸው ለማስገባት የሚናፍቁ በታማኝነት የሚያመልኩትና ፈቃዱን የሚሹ ሁሉ ኃይላቸውን ያድሳሉ ይላል የእግዚአብሔር ቃል። እግዚአብሔር በምንፈልገው ጊዜ ሁሉ የሚደርስልን እርዳታችን ነው። ልንታመንበት የሚገባ መልካም እረኛ ነው። ሊያድነንና ሊጠብቀን እስከ መጨረሻውም ከእርሱ ጋር ሊያቆመን የሚችል አምላክ ነው። ስለዚህ እናምልከው ልባችንንና ሕይወታችንንም ለእርሱ እናስገዛለት። ክብሩንና ገናናነቱንም ዘወትር እናውራ።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**